# የአማራ ብሔረተኝነትና የብ አ ዴን ሸፍጥ

ባንድ ወቅት ከኢ ሕ አ ፓ በተገነጠሉና ለወያኔና ሻአብያ አጎንብሰው ባደሩ ግለሰቦች ኢሕዴን ተብሎ የተመሰረተው ቡድን ታማኝ ሎሌ ሆኖ ገንጣዮቹ አዲስ አበባ በድል እስኪገቡ በድልድይነት በቅን አገልግሎዋቸዋል። በሽግግር መንግስት ምስረታም ሁሉም ጎሳዎች በተለያዩ ጎጠኞች ሲወከሉና አማራው ብቻውን አለተከራካሪና ተቆርቋሪ ሲቀር ይሄው ቡድን ተሰይሞ የነበረው በሕብረብሔርነት መልኩ እንደነበር ይታወቃል። ወያኔ አፈወርቂና የኦነጉ ሌንጮ አገሪቱን እነርሱ በሚፈልጉት ቅርጽ ሲበጣጥሱና ትግራይን፤ ኦሮሞውን ወዘተ. ተጠቃሚ አድርገው ወሎን፤ ሸዋን፤ ጎጃምንና ጎንደርን ሸንሽነው አናሳ ሲያደርጉና አማራው ብጣቂ መሬት ላይ እንዲቀመጥ ሲወስኑ ማንም አይዞህ አለሁልህ ያለው አልነበረም። ለዚህም የአማራው ቀንደኛ ጠላት መለስ በግዜው በኢቲቪ ሽግግሩን በሚመለከት "አማራውን እወክላለሁ ብሎ የመጣ ድርጀትም ሆነ ግለሰብ አልነበረም" ብሎ የተናገረው በአዲስ ዘመን ላይ የወጣ ሲሆን የቪድዮ ማስረጃው ደግሞ እስካሁንም በዩቲዩብ ላይ ይገኛል።

ታዲያ ሀቁ እንደዚህ ሆኖ እያለ ክልል ተብለው በሽግግሩ የተመሰረቱትን ግዛቶች የውስጥ አስተዳደር እንዲመሩ ሁሉም ጎጠኞች ቅርጫ ሲገቡ ውክልናና አቅሉን አጥቶ የአማራ ክልል በሚል የተሰየመውን አካባቢ የሚያስተዳድረው ሲጠፋ ወያኔና አጋሮቹ ኢሕዴን በሀላፊነት ተረክቦ ሕወሐትና ሌሎቹ በሚፈልጉት መንገድ እንዲመራው ርክክብ ተደረገ። ይህ እንደሆነ ዶሮን ሲያታልልዋት. . . ሆነና የፖለቲካው ጨዋታ ሎሌዎቹ ብ አ ዴ ን የሚል ስም ይዘው ባህርዳር ላይ ብቅ አሉ። ዋኖቹና አብላጫውን የስራ አስፈጻሚና ማእከላዊ ኮሚቴ መቀመጫ የያዙት ትግራይ/ትግርኝ፤ ከምባታ፤ ሐድያ፤ ሲዳማና ኦሮሞዎች ነበሩ። ከነርሱም ጋር ጥቂት የአዊና ዋግ አገዎች ነበሩባቸው። ዛሬ ላይ በጤና፤ በት/ት፤ በመንገድ፤ በሙብራትና ንፁህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት በአጠቃላይ በልማትና የድህነት ቅነሳ አማራ በአገሪቱ የመጨረሻው ጭራ ላይ እንዲቀመጥ የተደረገው ለምን እንደሆነ ጥናትና ምርምር ማድረግ አያሻም። ከመላው የአገሪቱ ክፍሎች መጤ እየተባለ የሚወገረውም በራሱ ልጆች የማይተዳደር ስለሆነ እንደሆነ ጠንቅይ መቀለብ የለብንም።

ይህ የሰይጣኑ ወያኔ ደቀ መዝሙር ብ አ ዴ ን አማራውን ገዝግዞ እንዴት እያጠፋው እንዳለ ሁላችሁም የምታውቋቸውን ዝርዝሮች አንድም ሳይቀር በሞረሽ፤ በቤተ አማራ፤ በመላው አማራ፤በአዴሀን፤በወልቃይት ታጋዮች፤በጎበዝ አለቆች፤በልሳነ አማራ፤በአሜሪካ የአማራ ማህበር፤ በአክቲቪስቶች፤ቁጥር ስፍር በሌላቸው ታሪክንና የወቅቱን በኢትዮጵያ የአማራውን ብሶት ቁጭ አድርገው በሚያሳዩ ትንተናዎች በተለያዩ ድህረ ገጾች በተለይም በወልቃይት.ኮም፤በኢትዮ

ፓትሪዮትስ፤ በዘሀበሻና ናዝሬት.ኮም፤ ወዘተ. አይተናቸዋል፡ አንብበናቸዋልም፡ በየግዜው በቃለ መጠይቅ ይዘታቸውም አድምጠናቸዋል። አሁንም፡ ነገም፡ ተነገድያም፡ ይሄው አማራውን የማንቃቱና ተደራጅቶ ህልውናውንና ማንነቱን እስከሚያስከብር ድረስ ይቀጥላል፤በአማራው ሁሉ መወደስ ያለበት እንቅስቃሴ ቢሆንም፤ አሁን ላይ ግን ከዚህ ዓይነቱ ትግል ባሻገር ማየት የሚያስችል ተግባራዊ አቅም መፍጠር የአማራውን ተጋድሎ ስለሚጠብቀው የታጋዮችን ስልት ወደ መልስ ምት ማዞር ለአማራው የግድ ይሆናል። በይሉንታ ምንም ሳይከላከሉና ጠላትን ሳይጋፈጡ ሁልግዜ መጨፍጨፍና መፈናቀል ራስን ከማጥፋት የባሰ አሳፋሪ የሞት ሞት ነው።

በተግባር ትግሉ አልተንቀሳቀሰም ማለት ፈጽሞ አይቻልም። ለምሳሌ በነ ወልቃይት ጉዳይ የተቀጣጠለው የአማራ ማንነት ትግል ፍሬውን አፍርቶ በዚች ሶስት ዓመት ውስጥ በጎንደር በተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች፤ በጎጃምም እንደዚሁ በተለይም በባህርዳር፤ በወልዲያ፤ በቆቦና መርሳ የአማራ ብሔረተኝነትን ባቀነቀኑና በውድ ሕይወታቸው በአረመኔው ወያኔና ብ አ ዴ ን ነፍስ በላዎች ወንድምና እህቶቻችንን በግፍ አጥተናል፡ አሁንም ድረስ እያጣን ነው ያለንው። በሸዋም ውስጥ ውስጡን በወያኔዎች በግፍ የታጨዱ ግን በገሀድ ያልተወራላቸው አማሮች በርካታ ናቸው። ስንቱ አማራ እንደወጣ/እንደወጣች ቀርተዋል? ሀቁ እስኪወጣ ድረስ ቤት ይቁጠራቸው። እነ ጎቤንና ሌሎች የጎበዝ አለቃና ጭፍራዎችን እንዴት እንረሳለን!!! “አማራ የለም፤ የአማራን ብሔረተኛነት እናወድመዋለን፤. . .”ወዘተ. ለሚሉን ጠላቶች ሁሉ አማራው መኖሩንና ስለማንነቱም ምንም ሳያወላውል መስዋዕት እየከፈለ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቶ አሳፍሮ ኩምሽሽ አድርጎአቸዋል። "አማራ አልነቃም! አልተደራጀም! አልታጠቀም!” ለሚሉትም ቀስ በቀስ ባገር ውስጥና በውጭ አገርም "አማራ ነኝ!” በሚል እየተደራጀና አቅሙን በየቀኑ እያሳደገ ጠላቶቹን መጋፈጥ መጀመሩን ሲያዩ የሚይዙትንና የሚጨብጡትን አጥተው በአሉባልታ ብቻ የአማራውን ተጋድሎ አቅል ለማሳጣት ሲንደፋደፉና ሲያላዝኑ የሚታዩበት ምዕራፍ ላይ ትግሉ ደርስዋል። ይህም ተጨማሪ የአማራ ብሔረተኝነት ያስከተለው አዎንታዊ ውጤት ነው።

በአማራው መፈናቀል ዙሪያ የተደረገውና የሚካሄደው እልህ አስጨራሽ ቅስቀሳና ትብብርን መቐቐም ያልቻለው ጸረ አማራው መንግስት በመጠኑም ቢሆን የተፈናቃዩ ብሶት በአማራና አዲስ አበባ ባለው የወያኔ ቲቪ ሳይቀር ዜና ሆኖ እንዲወጣ አስገድዶታል። የሕሊና እስረኞች እንዲፈቱ በተከታታይ የተደረጉ ጉትጎታዎች ዛሬ ላይ ተሰምተዋል፤ በርካታ የአማራ ልጆች ተለቀዋል። ለዚህም ልሳነ አማራና ቤተ አማራ እንደዚሁም ወልቃይት.ኮም ወዘተ. ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛና በአማራው ተጋድሎ ልዩ ስፍራን የሚያሰጣቸው ነው። በዚህ ጉዳይ በግል የአክቲቪስቶች ሚናም ቀላል አይደለም። በጣና ሀይቅ እምቦጭን ከማስወገድ አኳዋያ ብ አ ዴንና ወያኔ ሆን ብለው ቢተኙበትም አማራው እንደ ንብ ዘሞ በመጮሁና ገንዘቡን አውጥቶ ጠራጊ ማሽን እስከ መግዛትና በጉልበቱ በመረባረቡ ያፈሩት ግፈኞቹ ገዢዎቻችን ሳይወዱ በግድ ለመተባበር ሀፍረታቸውን ውጠውና ተሸንፈው ባደባባይ ተቆርቐሪ መስለው ብቅ እንዲሉ ተገደዋል። ይህ ለአማራው ብሔረተኛነት በአገርም ከአገር ውጪም ላለው አማራ መቀራረብንና መተዋወቅን የፈጠረ አንድ ታላቅ ድል ነው ማለት ይቻላል።

ከእንፉቅቅ ወደ መራመድ መሸጋገር የጀመረውን የአማራ ብሔረተኛ ትግል ለማኮላሸት ያለው ሰይጣናዊ መንግስት ዛሬ ላይ ውስጥ ውስጡን ደባ መፈፀሙን ለማፋፋም ስልቱን ቀይሮ ብቅ እንዳለ በቂ ማስረጃዎች መታየት ጀምረዋል። ሁላችንም ብአዴን በአማራ ልጆች እንደማይመራ እናውቃለን። ስለዚህም የዚህ አፀያፊ ፀረ አማራ ቡድን እንዝርት የሆኑት በረከትና አዲሱ ክፉኛ በመስጋታቸው እስከ ዛሬ የአማራውን ጭንቅላት እንዲመታላቸው ያስቀመጡትን አለምነው መኮንን የሚባል ብትራቸው በአማራው ብሔረተኝነት በተደረገበት እልህ አስጨራሽ የማጋለጥ ቅስቀሳ እንደ ቀድሞው ሊያገለግላቸው እንደማይችል ስለተገነዘቡና ባጥቃላይ በአማራው ሁሉ መጠላቱን ስለተረዱ ከፓርቲያቸው መከላዊ ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ሀላፊነት አስነስተው ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ አሸሽተውታል። ይህኛው ደግሞ ሌላኛውና የአማራ ብሔረተኛነት ተጋድሎ የድሎች ድል ነው ማለት ይቻላል።

በረከትና አዲሱ በዚህ ብቻ አላበቁም፡ ባህርዳር ላይ እንደ አለምነው የሚሆንላቸው ስለማያገኙ አዲስ አበባ ላይ ለገሰ ቱሉን በብአዴን ላይ በውስጠ ታዋቂ ጭነው የአለምነውን ጥፋት በቀጣይ እንዲከውንላቸው ዕቅዳቸውን ዘርግተዋል። ትዝ ካላችሁ ለገሰ ቱሉ ማለት የኦህዴድና ኦነግ ዓላማ አንግቦ በብአዴን ውስጥ ተሸሎክልኮ መርዝ ሲረጭ የኖረ ተኩላ ነው። አያሌው ጎበዜ የክልሉ መሪ በነበረበት ወቅት የአማራ መገናኛ ብዙሀን የሚባለውን የወያኔ የቅስቀሳ መስሪያ ቤት በሀላፊነት ያስተዳድር ነበር። በዛን ወቅት የአማራ ቲቪ ክፍልን በወያኔ ሰላዮች አስወርሮ እስከዛሬ ድረስ አማራ የትግሬዎች መፈንጫ እንዲሆን የተንኮል ሴራ የገመደ ፀረ አማራ የሆነ የኦሮሞ ተወላጅ ነው። ሰውዬው የበረከትና በተለይም የአዲሱ የቀኝ እጅ ሲሆን ከአያሌው ጎበዜ ጋር መግባባት ባለመቻሉ ከባህርዳር ተነስቶ አዲሱ ይመራውና ያስተዳድረው በነበረው "የመለስ አካዳሚ" በሚንስትር ደዔታ ማዕረግ ተሹሞ እንዲዛወር መደረጉ ይታወቃል። አሁንም እዛው ሲሆን የአለምነው መኮንን ምክትል ሆኖ "አካዳሚውን" መምራቱን ቀጥሎ ይገኛል። ልብ ካላችሁ አዲሱና በረከት ሁለቱን ፀረ አማራዎች ማለትም ለገሰ ቱሉንና አለምነውን አንድ ላይ ያደረጉዋቸው ተባብረው በአማራው ላይ አጥፊ ተልዕኮ እንዲሸርቡላቸው ያቀናበሩት ዘዴ ነው። እነዚህ ሽማግሌዎችና ካሳ ተ/ብርሀን፤ ጎላዊ ዮሴፍ፤ ደመቀና አለምነው፤ ተካ ቱሉና ሌሎቹ ከፍተኛ አመራሮች የሚባሉት የብአዴንና አማራ የማይሽር ነቀርሳ ናቸው።

ለገሰ ቱሉ በተለይም በሰሜን ሸዋ አማራዎች ላይ በወያኔው ብ አ ዴ ን በሚፈፀመው ደባ ሁሉ ቀጥተኛ ተሳታፊ ነው። የደብረብርሀን ዩኒቨርሲቲ የቦርድ ሰብሳቢ ስለሆነ ት/ት ቤቱ በትግሬና ኦሮሞዎች ከታች እስከ ላይ ተውተብትቦ እንዲጠፈር ያደረገና ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ በት/ት ቤቱና ሸዋ አማራ ላይ እያደረሰ ይገኛል። በሰሜን ሸዋ ለርሱ ያላደረ የብ አ ዴ ን አባል በሀላፊነት አይቀመጥም፤ ይህንን ደግሞ አዲሱና በረከት እንደዚሁም ኦህዴድና ኦነግ ይደግፉለታል። በርሱ አመለካከት ሰሜን ሸዋ ኦሮሞ እንጂ አማራ አይደለም። በቅርቡ ብ አ ዴ ን የጥልቅ ተሀድሶና ቅብንጥርሶ እያለ ባከታታይ ባደረጋቸው የማዕከላዊ (እነርሱ የበላይ አመራሮች የሚሉት) ስብሰባን ተከትሎ መጠነኛ የሰው የቦታ ሽግሽግ ሲያደርጉ ለገሰ ቱሉን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ወደ ስራ

አስፈጻሚነት አሳድገውታል። ይህም የሆነው በበረከትና አዲሱ ግፊት ነበር። ሹመቱን እንዳገኘ በፍጥነት ወደ ተልዕኮው እንዲገባ በሽማግሌዎቹ የአማራ ጠላት የብ አ ዴ ን መዘውሮች ትዕዛዝ ደርሶታል።

ለገሰ ቱሉ በመርዝ በተለወሰው የእባብ ምላሱ ግንቦት 18 ና 19 አዲስ አበባ ባለው ፓርላማ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራርየሚባሉትን ሰብስቦ አመራር ሰጥትዋል። በስብሰባው ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ የቀረበው ሊያቆሙት ያልቻሉትን የአማራ ብሔረተኝነት ለመሰባበርና ይሄው እንቅስቃሴ ወደ ኦሮሚያ ልትዛወር መንገድ ላይ በወያኔ እንድትገባ በተደረገችው አዲስ አበባ ያለው አማራ በማንነቱ እንዳይነሳ ባላቸው ሀይል ሁሉ ተጠቅመው ቅስሙን እንዲሰብሩትና እንዲያፍኑት ከወያኔ መንግስት ጋር ሌት ተቀን እንዲሰሩና እንዲረባረቡ የሚያሳስብና የሚያስጠነቅቅም ጭምር ነበር። በአፄ ዳዊት መዲና በአማራ ዕንብርት ላይ ለተሸረበው ጥፋት በረከትና አዲሱ ለገሰ ቱሉን ባደባባይ መጠቀም ጀምረዋል። እንግዲህ መላው አማራ ከፊታችን የተደቀኑትን የወያኔ ስርአትን እኩይ ጸረ አማራ ዕቅዶች ለማክሸፍ መረባረብ ይኖርብናል። ዶ/ር አብይ ጎንደርና ባህርዳር ላይ ፊት ለፊት በአካል ተገኝቶ ያየውን የአማራ ብሔረተኝነትን የበለጠ በማፋፋም ዱላን በዱላ፤ ጥፊን በጥፊ፤ ዕርግጫን በዕርግጫ ወዘተ. መጋፈጥ መጀመር ይኖርብናል። እስከ ዛሬ ተደብድበናል አሁን ደግሞ የመልስ ምት መስጠቱ ላይም እናተኩር። አማራን ሊያድነውም ሆነ ሊያጠፋውም የሚችለው አማራ ብቻ ነው። ይህን ስል ዝም እያልንና ነገር ያልፋል ብለን ላለፉት 27 ዓመቶች ጢቢ ጢቢ ሲጫወቱብን ዝም ብለናል፤ "እኛ ለአማራው ድምጽ ብቻ መሆን ነው የምንችለው" በሚለው ስልት ብቻ ከቀጠልን እንጠፋለን።

ሌላው አሳሳቢ ችግር ብአዴን በነከሌና እከሌ ቡድን ስለተከፈለ እከሌ ለአማራው ቀና ስለሚያስብ እናበረታታው ወዘተ. በሚል የሚደረገው ቅስቀሳ የአማራውን ብሔረተኛነት ተጋድሎ ውዥንብር ውስጥ እንዳይከተው ስጋቴን ለመግለፅ እፈልጋለሁ፤ በርካታ አማራዎችም በጉዳዩ ላይ ስጋት ብጤ እንዳላቸው ከሚሰጥዋቸው አስተያየቶች መገመትም ችያለሁ። ለማንሳት የፈለኩት ነጥብ ስለ ገዱ አንዳርጋቸው ነው። በደፈናው እርሳቸውን ለመውቀስ ሳይሆን እንዲያው ስልጣን ላይ ከመጡ ወዲህ የተፈጠሩትን የማይካዱ ሀቆች በትንሹ ላሳያችሁ።

1/ጣና በእንቦጭ ተወሮ ያካባቢው ገበሬና የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሁለት አስተማሪዎች መካከል ዶ/ር አያሌው ወንዴ የክልሉ መንግስት ለምን ዝም ይላል ሀይቁ እንዳይጠፋ አንድ ነገር አድርጉ ብለው አምስት ዓመት ሲጮሁ የገዱ ምላሽ ዝምታ ብቻ አልነበረምን? ማስረጃው እኮ በአማራ ቲቪ ተዘግቦ ይገኛል። 2/የትግራይ ታጣቂዎች እንደልባቸው ወደ ክልሉ እየገቡ አማራውን አበሳ ሲያሳዩት ገዱ ያደረጉት መከላከልስ ነበረን? ለምሳሌ በወልቃይት ጉዳይ ጎንደር ከተማ ታጣቂዎቹ መጥተው አማራን ሲገሉና ሲያፍኑ ይበቃል ብሎ የመከላከያ እርምጃ የሰጣቸው ኮለኔል ደመቀ አይደለምን?(አንድ ጀግና ከጦር ሰራዊት የተሰናበተ ታጋይ) 3/በዚሁ የወልቃይት የአማራ ጀግናችን በተቀሰቀሰው የአማራ ማንነት ተጋድሎ ወያኔ ኢጋዚን በክልሉ አሰማርታ በጎንደር በባህርዳር፤ በሌሎችም የአማራ ቀበለዎችና በቅርቡ በወልዲያ፤ በመርሳና ቆቦ ወጣቱንና ታዋቂ አማሮችን

ስትጨፈጭፍ የአቶ ገዱ ሚና አማራውን አድኖትስ ነበር? እስከማውቀው ድረስ ገዱና አፈ ቀላጤው የአማራውን ብሔረተኝነት ተጋድሎ "ብሔር ተኮር ጥቃት ስለሆነ ንብረታቸው ለወደመና ሸሽተው ለወጡ ትግሬዎች የክልሉ መንግስት ካሳ ይከፍላል፤ ተፈናቃዮችም ተመልሰው እንዲመጡ ይደረጋል" ማለታቸውን ነው። ለመሆኑ በግፍ ለተገደሉት የአማራ ልጆች ቤተሰቦችና በ 27 ዓመት ውስጥ ለተጨፈጨፉትና ተባረው ንብረታቸውን ላጡት አማራዎችስ እነ ገዱ ምን ያደረጉት ይኖር ይሆን? ይሄን ጥያቄ የርሳቸው አቀንቃኞች ምላሽ ቢሰጡበት የሚያሻ ይመስለኛል። ከተሳሳትኩ ደግሞ ደጋፊዎቻቸው በማስረጃ አመላክተው ሊያርሙኝ ይችላሉ። 4/ ማነው ግጨውንና በዛው አካባቢ ያለውን መሬት በእጁ ፈርሞ ለዛውም በዚህ ዓመት ለትግራይ ያስረከበውና "የድንበሩን ችግር ለአንዴና መጨረሻ ፈተነዋል" ብሎ በአማራ ቲቪ ሲናገር የሰማነው? አቶ ገዱ አይደለምን? "ከዝንጀሮ ቆንጆ. . .” እንደሚባለው አንድ ሰውን ጎላ አድርጎ በማዳነቅ እየተሰራ ላለው ቅስቀሳ የገዱ የስራ ውጤቶች ወይም (record) ዓይቶ ፍርድ መስጠት ስለሚሻል ብአዴንን ይዘንው እንታገላለን ለሚሉ የአማራ ልጆች እስቲ ረጋ ብላችሁ አስቡበት ለማለት እወዳለሁ። እዚህ ላይ ምላሻችሁን በአማራ ጨዋነት ላይ ተመርኩዛችሁ ከዘለፋና ተራ ስድብ ውጡና ገዱ ለአማራው ተጋድሎ ያስፈልገዋል የምትሉበትን ተግባራዊ ማስረጃ አንድ፤ ሁለት፤ ወዘተ. እያላችሁ ለኔም ሆነ ለአማራው የማናውቅወን እንኩ እንድትሉን እጋብዛለሁ።

ብ አ ዴ ን ባለፉት አስርና አስራ አምስት ዓመቶች በርካታ የአማራ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለኑሮ ሲሉ ሳይወዱ ተገደው በአባልነት ተፈርጀውበታል። የነዚህ የተማሩ አማራ ወጣቶች ኑሮ በየቀኑ በገሀነም እሳት እንደመገረፍ ይቆጠራል። በአመራር ላይ እንዲቀመጡ አያስፈልግም፤ ግን አመራሩ ቁንጮ ላይ ያሉት የወያኔ ካባዎች መገልገያና መጠቀሚያ ሆነው ቀርተዋል። በነፃነት ትንፍሽ የማለት መብት የላቸውም። እነዚህ ወገኖች ለአማራው ይቆረቆራሉ፤ በሚደርስበት በደልም ይቆጫሉ ሆኖም አቅም ስለሌላቸው ቆሽታቸው እየደበነ በማጉረምረምና በዝምታ ባርነትን ይገፋሉ። ለዚህምነው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወደ ውጪ ወጥተው የማይመለሱት። ስለዚህ በደፈናው ብ አ ዴ ን ውስጥ አማራነት የሚያንገበግባቸው የሉም ማለት የማይቻለው። ዞሮ ዞሮ ግን እንደ ድርጅት ከስር መሰረቱ አማራን ገዝግዞና በጣጥሶ ለማጥፋት በወያኔ ነፍስ የተዘራበትና ከሕወሐት ውጪ መሆን ስለማይችል፤ ድርጊቱና አመራሩ አማራዊ ቅርጽና ይዘት ስለሌለው ድርጅታዊ መዋቅሩ ይፍረስ ከሚለው ጎራ ራሴን ያስገባሁት።

በአጠቃላይ በውስጡ ላሉ ንፁህን የአማራ ልጆች ልናዝንላቸው፤ ልንደግፋቸውና ከአማራው ብሔረተኛ ትግል ጎን እንዲሰለፉና አጋር እንዲሆኑ እርዳታችን ሊነፈጋቸው እንደማይገባም አምናለሁ። እነዚህን ወጣቶች ወያኔ ነበርክ/ነበርሽ በሚል ቀልባቸውን መግፈፍ ተገቢ አይደለም። ወያኔን ኖረውታል፤ ዓይተውታል፤ ከስር መሰረቱ ያውቁታል፤ በአማራነታቸው የግፉ ተቋዳሽ ሆነዋል፤ እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትነዋልና ከነርሱ ጋር ተባብረን አማራን ለመታደግ ብንሰራ ሊጠቅመን ይችላል፡ እዚህ ላይ ግን ከመካከላቸው አንዳንድ ሊለወጡ የማይችሉና በጥቅም ከወያኔ ጋር የተቆራኘ ህይወት ላይ ያሉትን ሰላዮች አንሻዋሎና ነጥሎ ማጋለጥንም ማወቅ አለብን። "አሳን መብላት በብልሀት" ባጭሩ የአማራ ተጋድሎ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ

መዘናጋትም የለብንም።

የለም ራሳችንን ለማዳን በአማራነታችን ተደራጅተንና ታጥቀን የሚያጠቁንን እኛም እናጥቃቸው ብለን ከተነሳን እነርሱም እኛን ሳይወዱ ከመናቅ ወደ ማክበር እንዲዞሩ ስለሚያስገድዳቸው በኛነት ወይም በአማራ ብሔረተኝነት ከመሰባሰብ ውጪ ምንም ሌላ መፍትሄ አይኖረንም። መሬት ላይ የወረደ ስራ እንስራ። ባላገሩን ልንደርሰውና በማንነቱ የተጋረጠበትን የጥፋት መሰሪ ተንኮል እንዲረዳው እናድርግ። ብ አ ዴ ን የሚገዘግዘውና የሚያጠፋው እንጂ ለርሱ የሚቆረቆር እንዳልሆነ እስኪገባው በማስረጃ እናስተምረው። ዋነኛው ተጠቂው ይህኛው የአማራ ሕዝብ ነውና። ውጪ ያለው ተወቃቅሶና ተማምሮ እዚህ ተደርስዋል። ይሄው ሁኔታ አንድ መግባባት ላይ እስኪደረስ ከዛም በሁዋላ ይቀጥላል። በብሔር መደራጀትን የተቀበለውም ያልተቀበለውም ግን በአማራነቱ ብቻ አገር ቤት የመከራው ደውል በየቀኑ ለሚንቃጨልበት ወይም ለሚደወልበት ምስኪኑ የአማራ ገበሬ፤ ወጣት፤ ነጋዴና ሌላውም በወሬ ብቻ ሳይሆን አሁን ላይ እንደተጀመረው በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ አይዞህ እያልንው ወደ አማራ ማንነቱ እንዲዞርና እንዲታገል ምሶሶ እንሁነው። ይህን የማድረግ አቅም ያለን መሆኑን ራሳችንን ስንጠራጠር የነበርንው ሁሉ በጣና ላይና በተፈናቃዮች በተሰራው ተግባራዊ አማራነት ዓይተን መስክረናል። ቁም ነገር ያለውን ትግላችንን ወደ የሚናከስ ጥርስ ማሸጋገር እንችላለን። ዝም ብለን አንመታ! እኛም እንደ ጠላቶቻችን የሚማታ ትውልድ እንፍጠርና ጎልውናችንን እናስመልስ!!! ሁሉን አቀፍ አደረጃጀት በእጅ የሚለን የትግል ወቅት ላይ ደርሰናል።

በመጨረሻም የአማራው ብሔረተኛነት ተጋድሎ ግንቦት 20 ና ብ አ ዴ ን የአማራው ውድመትና ጥፋት መሆናቸውን እያንዳንዱ አማራ በተለይም አገር ቤት ያለው በጥልቀት ተርድቶ በትግሉ ውስጥ ቆራጥና ወሳኝ ሚና መጫወት እንዲችል አዲስ የትግል ስልት ቀርጾ መንቀሳቀስ መጀመር ይጠበቅበታል። ስለዚህም በሁለቱም የአማራ ጠላቶች ላይ ያነጣጠረና ያላሰለሰ የቅስቀሳ ዘመቻ በአክቲቪስቶችና በአድማስ ውስጥ በታቀፉ ሀይሎች ልዩ ትኩረት ይሰጠው!!!

በማር የተለወሰው አዲሱ የወያኔ አስመሳይ ኢትዮጵያዊ ቅስቀሳ የአማራውን ብሔረተኝነት ትግል እንዳያዘናጋው ከሌሎች ግዜዎች በበለጠ ፈታኝና ውጣ ውረድ የሚበዛው የፖለቲካ አውራ ጎዳና መጠርጉን እያንዳንዱ የተጋድሎው አካል ተገንዝቦ አማራውን ለማዳን ከምን ግዜውም በበለጠ ብልህነትን፤ ኮስታራነትንና የማያወላውል ቆራጥ ስራ ከሁሉም አማራ የሚጠበቅበት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ተደርስዋል። በዚህ የወያኔ ስልት ቀስ በቀስ ከአማራው ተጋድሎ የሚሸሹና አንድ በአንድ በየፎርማታው(ጣቢያው) የሚወርዱና የሚንጠባጠቡ ይኖራሉ። የአማራው ተጋድሎ ልክ እንደ ሽንፍላ ግዜውን ጠብቆ በደንብ ታጥቦና ፀድቶ የሚጠራበትም ወቅት ስለሆነ ማን ማን እንደሆነ ለመለየት ሳንቸኩል የምናየው ይሆናልና "የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል. . ." ስልቹነትን አስወግዶ በአማራ ብሔረተኛነት ትግል መጎልበት ላይ ተስፋ ሳይቆረጥ ርብርቦሽ ያሻል። አማራ ከጥፋት የሚድነው አሁን ያለው ሥርዓት ሲለወጥና ሲያከትም ብቻ ነው።

አብነት ሁነኛው ነኝ!!!